# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 2 ቁጥር 62 ህዳር 2 ቀን 2013ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ



## < <የትግራይ አጣ ፋንታ የሚወሰነው በትግራይና በኢትዮጵያ ሕዝብ አንጂ በተሸነፈ ኃይል አይደለም ! > >

ሀብታሙ ኪታባ

# ቆይታ

## «የትግራይ እጣ ፋንታ የሚወሰነው በትግራይና በኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ በተሸነፈ ኃይል አይደለም!»

ሀብታሙ ኪታባ

ሀብታሙ ኪታባ የኢዜማ የዕጩዎች ምልመላ ኮሚቴ አባል፣ የሥልጠና እና የአቅም ግንባታ ኃላፊ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፖሊሲ አዘጋጅ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአካውንቲንግና ፋይናንስ የመጀመሪያ ድግሪ፣ በቢዝነስ አድሜንስትሬሽንም ሁለተኛ ዲግሪ አላቸው፡፡ ሀብታሙ ኪታባ የፖለቲካ ተሳትፏቸውን በኢዜማ ምሥረታ ውስጥ አሀዱ ብለው የጀመሩ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በፓርቲው ውስጥ ጉልህ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከተመረቁ በኃላ ለስድስት ወራት ያህል በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ከሠሩ በኋላ በዓለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅቶች ውስጥ ለአሥርት ዓመታት ያህል በሥራ ዓለም ውስጥ ቆይተዋል፡፡ በአሁን ወቅት በከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች በሀገረኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የአካውንቲንግ ትምህርትን አጋዥ መጽሐፍት በማዘጋጀት ለሕትመት ለማብቃት ጥረት እያደረጉ ነው፡፡ በተጨማሪነትም በሀገራችን በአክሲዮን ሥራ ላይ የተሳተፉ የሀገሪቱን ዜጎች በማማከር ላይ ሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡ የዚህ ሳምንት የዜጎች መድረክ «የቆይታ» አምድ እንግዳ አድርገናቸዋል፡፡ ከእሳቸው ጋር ያደረግነው ቆይታ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡ መልካም ንባብ!



*ከለውጡ ማግስት በኋላ ከኢዜማ ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ እንዲሁም ከኢዜማ ምክትል መሪ አንዷለም አራጌ ጋር በመሆን ወደ መደ መቀሌ በመሄድ ሕዝባዊ ውይይት ማድረጋችሁ የሚታወስ ነው፡፡ በወቅቱ የመቀሌ ቆይታችሁ ምን ይመስል ነበር?*

መቀሌ በሄድንበት ጊዜ በሚነባስ ሆነን ቅስቀሳ ስናደርግ ሕዝቡ ፊት ላይ ድንጋጤን ማስተዋል ችለናል፡፡ ድንጋጤው የመጣው ሕወሓት ከሚያሳድረው ተፅዕኖ እና ከሚያደርገው ቁጥጥር የተነሳ ነው፡፡ በመዝናኛ ቦታዎች አግኝተውህ የሚነግሩህ ነገር የተለየ ነው፡፡ እሱን እንኳን ትተን ሚዲያዎች ከካሜራ ፊት የሚያወሩህና ከካሜራ ጀርባ የሚያናግሩት ፈጽሞ የተለያየ ነው፡፡ ፍርሃት ካልሆነ በስተቀር ሕዝቡ በሕወሓት ውስጥ ይገለጻል ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

በአዳራሽና ከአዳራሹ ውጭ ያለው ሁኔታም እንደሚለያይ አስተውያለሁ፡፡ አዳራሽ ውስጥ ተደራጅተው ነበር የገቡት፡፡ ከፌዴራል መንግሥት ጋር ያላቸውን ልዩነት የኢዜማን መድረክ በመጠቀም ለመግለጽ ሞክረዋል ፡፡ በጊዜው ካሜራ እንዲጠፋ ተደርጎ አንዲት እናት ወደ መድረክ ወጥተው በተፈጠረው ነገር በማዘን በለቅሶ ታጅበው ንግግር ያደረጉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

*መድረክ ላይ ወጥተው ያለቀሱበት ምክንያት ምንድነው?*

በብሔር ፖለቲካ ምክንያት የመጣባቸውን ጣጣ ለመግለጽ ነው፡፡ በአማራ ክልል ይኖሩ ነበር፡፡ በደረሰባቸው መፈናቀል ነው ስሜታቸውን የገለጹት፤ ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውን በማስመልከት «ወደ አካባቢዬ ወደ ንብረቴ መመለስ እፈልጋለሁ፡፡ እዚህ መጥቼም የረዱኝ ነገር የለም፡፡» በማለት የብሔር ፖለቲካ ያመጣባቸውን ችግር ነው የገለጹት ፡፡ «ኢዜማዎች መጥተዋል» ሲባሉ መፍትሔ እንድንሰጣቸው አስበው ነበር፡፡ ሌላ ልጨምርልህ መቀሌ ውስጥ መንገድ ጠፍቶኝ መንገድ ስጠይቃቸው የገጠሙኝ አማርኛ መናገር የማይችሉ የሀገሬ ሰዎች የምፈልገውን ቦታ ደስ በሚል መንገድ ነው ያሳዩኝ፡፡ ይሄ ከሌላ ቦታ የመጣ ነው ብለው በጠላትነት አልፈረጁኝም፡፡ አዳራሽ ውስጥም ከአዳራሽ ውጪም ያየነው ይሄንኑ ነው፡፡

*በሕዝቡ ዘንድ ምን አይነት አቀባበል ነበራችሁ? ሕወሓት እና የትግራይ ሕዝብ አንድ ናቸው በሚሉ የሚፈርጁ አሉ፡፡*

በማኅበራዊ እና በሌሎችም ሚዲያዎች ላይ «ሕወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ናቸው» ብለው ሲከራከሩ ይገርመኛል ፡፡ ሕወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ከሆነ ምርጫው ምን ያደርጋል? ሕወሓቶች «ምርጫው ጊዜውን ጠብቆ መደረግ አለበት» የሚሉትን ስትገለብጠው «እኛና የትግራይ ህዝብ አንድ አይደለንም!» ማለት ነው፡ ፡ እኛና የትግራይ ሕዝብ አንድ ስላልሆንን ሕዝቡ መምረጥ አለበት ብለው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስላስጮሁት አንስተን መከራከር የለብንም፡፡ ኢትዮጵያን የሚያክል ሀገር አንድ ፓርቲ የሕዝብ ነው ብሎ መናገር ፍትሃዊ ያልሆነ ነገር ነው፡፡ ሕወሓትና የትግራይ ሕዝብ አንድ ሊሆን አይችልም፡፡ አሁን ከሚደረገው ኦፕሬሽን በኋላ የሕዝቡን ስሜት የምናውቀው ይሆናል፡፡ ማሰብ ያለብን ሕወሓት ያለበትን አንድ መንደር ሳይሆን ሙሉ ትግራይን ነው፡፡

*በሕወሓት ላይ እየተወሰደ ያለው ሕግ የማስከበር ሥራ የድርድርና የውይይት አማራጮች ሙሉ ለሙሉ መፍትሔ መሆን አቅቷቸው ነው የሚል እምነት አሎት?*

ሕግ የማስከበሩ ሥራ ከመጀመሩ ከ48 ሰዓት በፊት «ሕወሓት ግጭት ውስጥ መግባት ለምን ፈለገ?» የሚል ጹሑፍ ጽፌ ነበር ፡፡ እያንዳንዱን ነገር ወደ ኋላ መለስ ብለህ ብታጤነው ሕወሓት ግጭት ውስጥ መግባት እንደፈለገ የሚያሳይ ነገር ነበር፡፡ ሕወሓት የሚሄድባቸው መንገዶች እንደ አንድ ተፎካካሪ ፓርቲ አልነበሩም ፡፡ ወደ ሀገር ጉዳይ እየመጣ ነበር፡፡ ግጭት ውስጥ መግባት ለምን ፈለጉ ብዬ ሳስብ እንደሚያሸንፉ ስላወቁ አይመስለኝም፡፡ በየትኛውም መንገድ የፌዴራልና የክልል መንግሥት ግጭት ውስጥ ገብተው የክልል መንግሥት ያሸነፈበት ታሪክ የለም ፡፡ ሕወሓት ትግራይ ውስጥ እንደ ከዚህ ቀደሙ እንደነበረው የሕዝብ ድጋፍ አለው ብዬ አላስብም፡፡ ስለዚህም ከፌደራል መንግሥቱ ጋር ግጭት ውስጥ መግባት የፈለገው በድርድር ሂሳብ በምርጫ የማያገኘውን ቦታ ለማግኘት ያለው አማራጭ ግጭት መፍጠር ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ ግጭቱ ሲጀመር የተለያዩ ኃይሎች «ግጭቱ ይቁምና እናደራደር» ይላሉ ፡፡ እሱ ከተሳካ ወደ መኃል እመለሳለሁ ፡፡ ወደ መኃል ከተመለስኩ ቀጣዩ ትልቁ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሕገ መንግሥት ማሻሻል ነው፡፡ በሕገ መንግሥቱ የማሻሻል ሂደት ላይ ትልቅ ሚና ይኖረኛል፡ ፡ የጀመርኩትን እቀጥላለሁ የሚል ሃሳብ ስላላቸው ነው ፡፡ ግጭቱን የፈለጉትም ለዚህ ይመስለኛል፡፡ አሁን ላይ ጥቃት የከፈቱት በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት የከፈቱት የሚፈልጉትን ነገር ስላጡ ነው፡፡

ኢዜማ ግጭት አስፈላጊ እንዳልሆነ ጉዳዩ ወደ ሰላም እንዲመጣ ብዙ ጥረት አድርጓል ፡፡ በመቀሌ ጉዟችንም ከክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ደብረ ጽዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር) ጋርም ውይይት አድርገናል፡፡ እኔ በዛ ውይይት ላይ በግሌ የተረዳሁት ነገር ርዕሰ መስተዳድሩ የፌደራል መንግሥቱና የትግራይ ክልል ግጭት ውስጥ እንዲገቡ እንደሚፈልጉ ነው፡፡ በእኔ ዕይታ የፌዴራል መንግሥት የሀገር አንድነትን ለማስጠበቅ ቀደም ብሎ አሁን ወደ ጀመረው ሕግ የማስከበር እርምጃ መግባት ነበረበት፡፡

*ሕወሓት የእርቅና የመደራደሪያ መንገዶችን አልቀበልም ብሎ አሁን ግን የፌዴራል መንግሥት የሀገር አንድነትን ለማስከበር ሕግ የማስከበር እርምጃ ሲወሰድ «እንደራደር» የሚል ሃሳብ አቅርቧል፡ ፡ የፌዴራል መንግሥት ድርድሩን እንደማይቀበል በግልጽ አሳውቋል፡፡ አንዳንድ አካላት በፌዴራል መንግሥት መልስ ላይ ቅሬታቸውን እያቀረቡ ጉዳዩን በሰላም ለመፍታት ዝግጁ አይደለም እያሉ ነው፡፡ በዚህ ላይ ምን አይነት ምልከታ አሎት?*

ሕወሓት ግጭት በመጀመር ድርድር ላይ የመቀመጥ ፖለቲካ ነው እየሰራች ያለችው፡፡ እዛ ላይ በመገኘት የሚሰጠውን የፖለቲካ ጥቅም ለመጠቀም ነው፡፡ ሕወሓት የተሸነፈ ቡድን ነው፡፡ ለሕወሓት የተሰጠው ቦታ ለትግራይ ሕዝብ ከተሰጠው ቦታ የመነጨ ነው፡፡ ከዛ ባፈለ ቅድመ ሁኔታ እያስቀመጡ ነው ድርድር የሚሉት፡፡ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ የማይችሉበት ቦታ ሆነው ቅደመ ሁኔታ ያስቀምጣሉ፡፡ ቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ «እፈልጋለሁ!» ግን «አልፍልግም!» እንደ ማለት ነው፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩት ቀጣዩ አጀንዳ የሕገ መንግሥት ጉዳይ ነው፡ ፡ ሕወሓት በመጣበት ቀመር ተመልሶ እንዲመጣ አያደርገውም፡፡ ስለዚህ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ነው ድርድር የሚፈልገው፡፡ አሁን ቅድመ ሁኔታውን ትቶ ድርድር እፈልጋለሁ ቢል ጊዜ መግዣ ነው፡፡ ዝም ከተባሉ በቀጣይም ሀገሪቷ ውስጥ እየተነኮሱ መደራደሪያ መድረክ ነው የሚያመቻቹት፤ የፌዴራል መንግሥቱ የያዘው አቋም ትክክለኛ ነው የሚል አቋም ነው ያለኝ፡፡

የፌዴራል መንግሥት የሕወሓትን ባህሪና ማንነት አይቶና ተንትኖ አለማምጣቱ በፌዴራል መንግሥት ላይ ያለው ቁመና ደካማ መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡ በእኔ እይታ ይሄ ቡድን መጥፋትና ከኢትዮጵያ ፖለቲካ መወገድ ያለበት ቡድን ነው፡፡ ሕወሓት ያደረገው በሊብያ በረሃ ላይ አሸባሪው የአይሲስ (ISIS) ቡድን ካደረገው የተለየ አይደለም፡ ፡ ልዩነቱ ሕወሓት በእኛ ሉዓላዊ መሬት ላይ እነሱ ደግሞ በሌላ ሀገር መሬት ላይ ማድረጋቸው ብቻ ነው፡፡

ሕወሓት ምርጫ አካሄጃለሁ ብሏል፡፡ የፌዴራል መንግሥቱ ደግሞ አልቀበልም ብሏል፡፡ የትግራይ ክልል መንግሥት አሁን ላይ ማን ነው ብለን መውሰድ እንችላለን?

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከማገዱ በፊት ሕወሓት ሕጋዊ መንግሥት ነበር፡፡ የፌዴሬሽን መንግሥት ለትግራይ ክልል ጊዚያዊ መንግሥት ይቋቋማል ብሏል፡፡ ስለዚህም አሁን ሕወሓት ሕጋዊ መንግሥት አይደለም፡፡

*ሕወሓት የሀገር መከላከያ ሠራዊትን ማጥቃቱ ሀገር እንዳጠቃ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ከዚህ አንጻር መከላከያ የሀገር አንድነትንና ሕግን ለማስከበር በሚወስደው እርምጃ ሕዝቡ እንዳጎዳ ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል?*

ይህ ጉዳይ ጥቅምት 26 ቀን

# አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

ህዳር 2 ቀን 20113 ዓ.ም
አዲስ አበባ

2013 ዓ.ም ኢዜማ በሠጠው መግለጫ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ሕግ ለማስከበርና የሀገር አንድነት ለማስጠበቅ የሚወሰድ እርምጃ ውስጥ ቄጤማ እያርከፈከፍክ አይደለም የምትሄደው፡፡ ፌዴራል መንግሥት በሚወስደው እርምጃ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ጠይቀናል፡፡ መንግሥትም ጥንቃቄ እያደረገ ሕግ የማስከበር ሥራውን እንደሚሰራ አሳውቋል፡፡ ሕግ የማስከበር ሥራ እየሰራ ሕዝቡን የመጠበቅ ሥራ ሊሰራ ይገባል ፡፡ ከዛ ይልቅ የሕወሓትን መንገድ ለቀው ሠራዊቱን እየተቀላቀሉ ያሉ ሰዎች ስላሉ ሕወሓት የመጨረሻ ተስፋ የመቁረጥ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡ የፌዴራል መንግሥት አደረገው ለማለት ሕዝብ ባለበት አካባቢ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ይሄን በማገናዘብ አንዳንድ ቦታዎች ላይ የተለያየ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

ቦታ ከኢትዮጵያ ነጥለን ልናየው አንችልም ፡፡ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ተነጥሎ የተለየ ጥቅም ይፈልጋል የሚል እምነት ፈጽሞ የለኝም፡፡ እንደውም በቀጣይ የኤርትራ ጉዳይ በኮንፌዴሬሽንም ይሁን ሌላ መንገድ ፈልገን አብረን መኖር አለብን ብዬ ነው የማስበው ፡፡ ቱሉ ቦሎ ችግር ተፈጥሮ የፌዴራል መንግሥት ቢገባ «የቱሉ ቦሎ እጣ ፋንታ ምንድን ነው?» ብለህ አትጠይቀኝም፡፡ ይሄ አጀንዳ እንዲሆን ለምን ፈለጉ ብለህ ካሰብክ ከዚህ ቀደም «መገንጠል እንፈልጋለን!» ብለው ያቀረቡት ሀሳብ የሚሆን መስሏቸው ነው፡፡ ይሄ የሚሆንበት ነገር የለም፡፡ የትግራይ እጣ ፋንታ ልክ እንደ አዲስ አበባ፣ እንደ አምቦ ሕዝብ ከኢትዮጵያውያን ጋራ አብሮ በሕዝብነቱ ይቀጥላል፡፡ «እኛ ሳንኖር ትግራይ አትኖርም!» የሚለው እሳቤ ሕዝቡን ስለማይወክሉት አያስኬድም!

ያንን ለመጠቀም ወደኋላ አትልም ፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያዊ ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለመግባት የሚፈልጉ ኃይሎች ቀደዳ የማይፈልጉበት ምንም አይነት ሁኔታ የለም ፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት ደኅንነቱን ማስከበር ይኖርበታል፡፡ ከዛ ቀጥሎ ከሌሎች ተቋማትና መንግሥታት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር ይገባል፡፡ ለፌዴራል መንግሥት ጥሩ እድል መጥቶለታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ሕወሓት ግጭት ውስጥ መግባት የፈለገው ከሕዝብ ጋር እንደሆነ አድርጎ ተቀብሎለታል፡፡ ይሄ በጣም ትልቅ እድል ነው፡፡ ይሄን ድጋፍ መጠቀም አለበት፡፡ ይሄን አስጠብቆ ለመሄድ ለሕብረተሰቡ በቂ መረጃ በመስጠት ሊጠብቅና ሕዝቡን ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ከሕዳሴ ግድቡ ጋር በተያያዘ የደኅንነት ጥበቃ መኖሩን እርግጠኛ መሆን እንድንችል ማድረግ አለበት፡፡

« ኢዜማም ሌሎች ፓርቲዎችም አቋማቸውን አሳውቀዋል፡፡ እንደዚህ አይነት አጀንዳዎች ላይ ሁሉም ተግባብቶ አቋም ይዞ ቢሆን ጥሩ ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢዜማ የወሰደው አቋቋም ትክክል ነው፡፡ የፓርቲ መድረክ ትርጉም እንዲኖረው ምርጫ ቦርድ ፓርቲ የሆነውንና ያልሆነውን የመለየቱን ሥራ ቢያፈጥነው ጥሩ ይሆናል፡፡ ብዥታ የፈጠረው የፓርቲዎች ቁጥር መብዛቱና ትክክለኛ በሀገር ጉዳይ ተጨንቀውና ተጠበው አቋም የሚይዙ ውስን ፓርቲዎች ብቻ በመሆናቸው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡»

*የፌዴራል መንግሥት እየወሰደው ያለው የሀገር አንድነትን የማስጠበቅና ሕግ የማስከበር እርምጃ ሲጠናቀቅ የትግራይ ክልል እጣ ፋንታ ምን ሊሆን ይችላል?*

የትግራይ እጣ ፋንታ የሚወስነው በትግራይና በኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ በተሸነፈ ኃይል አይደለም፡፡ ለሕወሓት ያደሩ ሰዎች መከላከያ ሠራዊቱ ላይ ጥቃት የፈፀሙ ዕለት ነው፤ ሕወሓት የሞተው፡፡ ከዛ በፊት ሕወሓት በወረቀት ደረጃ የሚጫወት የፖለቲካ ፓርቲ ነበር፡፡

የኢትዮጵያና የትግራይ ሕዝብ አብሮ የኖረ፣ ብዙ ታሪክ ያለው ሕዝብ ነው ፡፡ ደብረ ፅዮን ገብረሚካኤል (ዶ/ር) አድዋ እዚህ ነው ሲሉ ነበር፡፡ በእርግጥ አድዋ እዛ ቢሆንም በአድዋ ጦርነት ወላይታው፣ አማራው፣ ኦሮሞው ሁሉም ብሔሮች ሄደው ተዋግተው፤ ሞተዋል፡፡ አድዋ ያለበትን

*አሁን ባለው የሀገር አንድነትን የማስጠበቅና ሕግ የማስከበር ሂደት ላይ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና የተለያዩ ሚዲያዎች ከሕወሓት በሚደርሳቸው መረጃ እና ፕሮፖጋንዳ ሕወሓትን የሚጠቅም ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ የፌዴራል መንግሥት አሁን እየወሰደ ያለውን ሕግ የማስከበር እርምጃ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በአግባቡ እያሳወቀ ባለመሆኑ በሕወሓት በኩል ብልጫ ተወስዶበታል፡፡ በቀጣይ በፌደራል መንግሥት በኩል ምን ዓይነት እርምት ሊወሰድ ይገባል?*

አሁን ላይ ባለው ሁኔታ የመንግሥትን ድክመት መነጋገር ተገቢ አይደለም፡፡ መንግሥት ድክመቱን ራሱ መሸፈን አለበት፡፡ ከፕሮፖጋንዳ በፊት ደኅንነቱን ማጠናከር አለበት፡፡ ለምሳሌ በዚህ ሁኔታ ላይ ግብፅ እድል የምታገኝ ከሆነ

የፌዴራል መንግሥት ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብን ከጎኑ ማሰለፍ አለበት ፡፡ አንዳንዱ ፍላጎት ኖሮት ኃይል ላይኖረው ይችላል፡፡ ማን አቅም አለው? ማን ነው ፍላጎት ያለው? ሁለቱም ማን አለው? ለማን ምን አቀርባለሁ? የሚለውን መተንተን አለበት ፡፡ ዲፕሎማቶችን ጠርቶ ከማናገር ባለፈ ማን ላይ ምን ማድረግ አለብኝ? የሚለውን ማወቅ እና ደኅነነት ላይ መሥራት አለበት፡፡

*ኢዜማ በፓርቲዎች በጋራ ምክር ቤት በኩል የተሰጠውን መግለጫ እንደማይቀበል ይፋ አድርጓል፡፡ ኢዜማ ከመከላከያ ጎን መቆሙና የጋራ ምክር ቤቱ መግለጫ መለያየቱ ብዙ ሰዎችን ግር አሰኝቷል፡፡ አንባቢያን እንዲረዱት ይህን ጉዳይ ግልጽ አድርጉልን፡፡*

አንድ መታሰብ ያለበት ነገር የፖለቲካ ፓርቲዎች መድረክ መሥራቾቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ አሁን





ባለው በእኛ ሀገር ሁኔታ አምስት ሰውም የያዘ እንደ ኢዜማ ደግሞ ከአራት መቶ በላይ ምርጫ ወረዳዎችን ያቀፈ ፓርቲን የመለየትና የማጥራት ሥራ የምርጫ ቦርድ ነው፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ መሆን የሚያስቡ ግን በተግባር የፖለቲካ ፓርቲ ያልሆኑ አሉ ፡፡ የፖለቲካ ፓርቲ ሕዝብን ማታገል የሚችል ቁመና ያለው መሆን አለበት፡፡ ቢሮ ቁጭ ብለህ የሆነ ነገር ፅፈህ የምትለጥፍ ሳይሆን ሕዝብን ማታገል የምትችልበት ሃሳብ ያለህ እና ሃሳብህን ማስፈጸም የምትችልበት፣ ከሕዝቡ ጋር ደግሞ በቅርበት የምትገናኝ ፓርቲ መሆን አለበህ፡፡ ብልፅግናም ከኢዜማ ጋር ተቀራራቢ መዋቅር የለውም፡፡ ምናልባት የመንግሥትን መዋቅር እንደ መዋቅር ካልወሰድነው በስተቀር፤ ይሄ ደግሞ ስህተት ነው፡፡ ሌሎች ፓርቲዎች ቢደመሩ በእኔ እሳቤ ኢዜማን አያክሉም፡፡ ኢዜማ ለዚህ መድረክ ትልቅ ግብዓት ነው፡፡

ኢዜማ ያንን ስብሰባ በተመለከተ የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ልዩነት ሃሳቦች እንኳን ቢኖሩ በወጣው መግለጫ ላይ የሚስተናገድባቸው መንገዶች አሉ፡፡ ሕዝቡ የሆነው ይጠፋዋል ብዬ አላስብም፡፡ ኢዜማም ሌሎች ፓርቲዎችም አቋማቸውን አሳውቀዋል፡፡ እንደዚህ አይነት አጀንዳዎች ላይ ሁሉም ተግባብቶ አቋም ይዞ ቢሆን ጥሩ ነው የሚሆነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢዜማ የወሰደው አቋቋም ትክክል ነው፡፡ የፓርቲ መድረክ ትርጉም እንዲኖረው ምርጫ ቦርድ ፓርቲ የሆነውንና ያልሆነውን የመለየቱን ሥራ ቢያፈጥነው ጥሩ ይሆናል፡፡ ብዥታ የፈጠረው የፓርቲዎች ቁጥር መብዛቱና ትክክለኛ በሀገር ጉዳይ ተጨንቀውና ተጠበው አቋም የሚይዙ ውስን ፓርቲዎች ብቻ በመሆናቸው ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

*የትግራይ ሕዝብ ከሕግ የማስከበሩ እርምጃ ጋር ተያይዞ ምን ሊያገኝ ይችላል?*

የትግራይ ሕዝብ የሚያገኛቸው ሁለት ነገሮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ነጻነቱን ያገኛል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ማድረግ የሚችለውን እያደረገ ነው፡፡ የትግራይ ሕዝብ አጣብቂኝ ውስጥ ነው ያለው፡፡ ለምሳሌ አንድ ነገር ገጠመኜን ልንገርህ፡፡ መቀሌ በነበረን ስብሰባ ላይ አንድ ደብዳቤ ማተም ፈለግን፡፡ ደብዳቤው ስካን ለማስደረግ ወደ ኢንተርኔት ቤቶች አቀናን፡፡ ስካን አድርገን ማተም የፈለግነው ደብዳቤ ከለር ሆኖ እንዲወጣ ነው የፈለግነው፡፡ ኢንተርኔት ቤቶቹ ማኅተም ያለበትን ነገር ከለር ፕሪንት ማድረግ አይችሉም፡፡ ይሄ ትንሽ ነገር ቢሆንም አንድ ኢንተርኔት ቤትን እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ ያውቁበታል፡፡ ከለር ፕሪንት



« እዛ ውስጥ ያለው ነገር ምንድነው የሚናገረው? አጼ ዮሐንስ ከአፋር ጋር ያላቸውን ጉዳይ እንዴት ነው የፈቱት? አጼ ዮሐንስ የሄዱበት መንገድ አጼ ምኒሊክ ከሄዱበት መንገድ ምንድነው የተለየው? ቢለው ቢጠይቁ ይረዱታል፡፡»

ማድረግ አትችሉም ተብለው ተከልክለዋል፡፡ ይሄን ካደረግን እንጠየቃለን ብለዋል፡፡ በዚህ አይነት ደረጃ የሚገለጹ መዓት አፈናዎችና ጭቆናዎች አሉ፡፡

ሕወሓቶች የሰው ነጻነት የማይገባቸው ናቸው፡፡ ሕወሓት ቢወገድ የትግራይ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ጋር ተስማምቶ ይኖራል፡፡ ሌሎች ቦታዎች ሄዶ የመሥራት፣ የፈለገውን ፓርቲ የመምረጥ እድል ያገኛል፡፡ ነጻነቱንም ያገኛል፡፡

*ቆይታችንን ከማጠናቀቃችን በፊት የሚያስተላልፉት መልእክት ካለ እድሉን ልስጦት?*

ለሁለት አካላቶች መልእክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡ የመጀመሪያው ለትግራይ ወጣቶች ነው፡፡ ለትግራይ ወጣት የማስተላልፈው፣ ወጣት ማለት የሚጠይቅ ማለት ነው፡፡ የተሰጠህን ነገር ሁሉ ይዘህ የምትሄድ መሆን የለበትም፡፡ መጠየቅ የሚባል ነገር መኖር አለበት፡፡ የትግራይ ሕዝብ ሕወሓት ሳይኖር በፊት እንዴት ነበር የኖረው? የአጼ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት መቀሌ ውስጥ አለ፡፡ እዛ ውስጥ ያለው ነገር ምንድነው የሚናገረው? አጼ ዮሐንስ ከአፋር ጋር ያላቸውን ጉዳይ እንዴት ነው የፈቱት? አጼ ዮሐንስ የሄዱበት መንገድ አጼ ምኒሊክ ከሄዱበት መንገድ ምንድነው የተለየው? ቢለው ቢጠይቁ ይረዱታል፡፡ ይሄ መልዕክቴ የኦሮሞና የአማራን ወጣትም ይመለከታል፡፡ አሁን ካለው ነገር አንጻር ግን በተለየ ሁኔታ የትግራይ ወጣትን ይመለከታል፡፡

ሁለተኛው ኢዜማ ውስጥ ላሉ ወጣቶች ነው፡፡ ኢዜማ ያቀረበው ሀሳብ አሸናፊ ሀሳብ ነው፡፡ ኢዜማ በድንጋይና በጠመንጃ ሀሳቡን ለማስረጽ አይፈልገም፡፡ ኢዜማ የሚወያይባቸውና ያቀረባቸው ሀሳቦች ለኢትዮጵያ አሁን ላይ አስፈላጊ መሆናቸው የተረዳሁበት ወቅት ላይ እገኛለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ተስፋ እኛ አሁን የያዝነው አስተሳሰብ ነው፡፡ የዜግነት ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ነው? ማኅበራዊ ፍትህ ማለት ምን ማለት ነው? የሚሉትን የኢዜማ አባል ተረድቶ ማስረዳት ሲችል ነው የኢዜማ ሃሳብ ሕዝቡ ዘንድ ሊገባ የሚችለው፤ ይሄን እያደረግን በሄድን ቁጥር እያሸነፍን እንሄዳለን ብዬ አስባለሁ፡፡ የተሻለ ሀሳብ ቢዘገይም ይገዛል! (ጠብቆም ላልቶም ይነበብ) የኢዜማ ሀሳብ ሰዎች ሲገባቸው ነው የሚገዙት፡፡

*ለነበረን ቆይታ በአንባቢዎቻችን ስም ከልብ ላመሰግኖት እወዳለሁ፡፡*

እንግዳ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ እኔም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- ይህ ፅሁፍ የፀሐፊውን አቋም ብቻ ነው የሚወክለው!

# ትግራይ ፤ ሕወሓትና ቀጣይ ሁነቶች

በተክሌ በቀለ

## እንደ መግቢያ

በታሪካችን ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ልናገኝ ባለመቻላችን ከገዥዎች ጋር መተናነቅ የሕዝባችን እጣ ፋንታ ሆኖ ዛሬም ድረስ ዘልቋል፡፡ ከፀረ-አገዛዝ ጋር ከተደረጉት ትግሎች ውስጥ በቅርቡ የደርግን መንግሥት እስከ መለወጥ የደረሰው ትግል ውስጥ የትግራይ ሕዝብ ትግል ጎልቶ ይጠቀሳል ፡፡ በዚህ የትግል ሂደት ውስጥ ሕወሓት እና የትግራይ ሕዝብ በአንድነት ታግለዋል፡፡ በርካታ ድርጅቶች የትግራይን ሕዝብ ትግል በመቀላቀል ጭቆናን ለመታገል በወቅቱ ምርጫቸው የነበረ ቢሆንም በሴራም ይሁን በእውቀት ድርጅታዊ ቅርፅ በመስጠት በኩል የተሳካለት ሕወሓት መሆኑ አይካድም፡፡ በሂደትም የትግራይ ሕዝብ ትግል ምናልባትም ከመጠነኛ የቋንቋ ልዩነት በስተቀር ሁለመናው ተመሳሳይ በሆነው የአማራ ሕዝብም ሙሉ ድጋፍ በማግኘቱ በአጭር ዓመታት ውስጥ ሕወሓትን ለአራት ኪሎ አብቅቶታል፡፡ የአማራው ሕዝብ ትግል ባይታከልበት ኑሮ አራት ኪሎ ለሕወሓት ህልም ሆኖ ይቀር ነበር፡፡ አራት ኪሎ ሕዝብን የማስረሳት አዚም ኖሮት ይሁን አይሁን ባላውቅም ሕወሓት ከጅምሩ ፀረ-ሕዝብ ሆኖ የሁለቱን የሰሜን ሕዝቦች በደም የተፃፈ ትግል እንዲሁም የሌሎች ኢትዮጵያውያንን አስተዋፅኦ ገደል የወረወረው በመጀመርያ የመንግሥትነቱ ዓመታት ነበር፡፡ የኢትዮ-ኤርትራን ጉዳይ የቋጨበት አግባብ፤ የሕገ-መንግሥቱ ያለበቂ የሕዝብ ተሳትፎ ሲፀድቅ እና የሽግግር መንግሥቱን አንገት ቆልምሞ ሲጥለው ከተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝበ አይደለም ከትግራይ ሕዝብም ጋር ተቆራረጠ፡፡ በዚህ ላይ የዓይደር ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ሕፃናት ሳይቀር ህይወት የቀጠፈውን የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት እና ጦርነቱ የተቋጨበት አሳፋሪ ድርጊት በይበልጡኑ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ቆራርጦታል፡፡ ከዚያ ወዲህ በጉልበቱ ዓመታትን በስልጣን ላይ ቆጠረ፡፡

ሕዝብ ለትግል በመነሳሳቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ አቅም አጥሮት ከአራት ኪሎም እንደዘበት ለቆ ወጥቶ አሁን ያለበት ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ከመንግሥትነት ወደ አሸባሪነት ተዛውሮ የትግራይን ሕዝብ ጠባቂ ፤ ግብፅን ጨምሮ የውጭ ኃይሎችን ጥቃት ለመመከት ሌት ተቀን የሚሰራን የሃገር መከላከያ ሰራዊት በውድቅት ሌሊት አመራሮችን በመረሸን ጥቃት በማድረስ ከባድ መሳሪያዎችን በመዝረፍ በአደባባይ የሚፎክር ድርጅት ሁኖ ይታያል ፡፡ የሕዝቡ መራር ትግል የወለደው የሕወሓት/ኢህአዴግ የውስጥ ትግል ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዋለለት ውለታ ቢኖር ኢህአዴግን ማፍረሱ እና ሕወሓትን ከኢህአዴግ በግብር መነጠሉ ነው ብለው የሚያምኑ በርካቶች ናቸው፡፡ ለኔም ይህ እውነት ነው፡፡

## ሕወሓት እና ተቃዋሚነት

ድርጅቱ በተፈጥሮዉ ተቃውሞን ከልቡ አያስተናግድም፡፡ ሲፈጥረው ተቃውሞን የማስተናገድ እና የማቻቻል ታሪክ የለውም የሚሉት ብዙዎች ናቸው፡፡ ከውስጡ የሚፈጠሩ ቅራኔዎች ሁሉ የፈታው በጉልበት ነበር፡፡ ታሪኩ ይኸው ነው፡፡ በዚህ ድርጅታዊ ባህሪው መንግሥት ሆኖ አራት ኪሎ ገባ፡፡ በዚህ ባህሪው ሀገራችን ውስጥ ተቃውሞ ጎልብቶ፤ ሕዝብን ሊያማልል የሚችል ሀሳብ ፈልቆ ተተኪ ተቀናቃኝ እንዳይኖር በጉልበት፤ በሕግ፤ በገንዘብ ወዘተ ተቃዋሚው እንዲቀጭጭ እንዲበታተንም ከፍተኛውን መጥፎ አሻራ አኑሯል፡፡ ተቃዋሚው አሁን ለሚገኝበት ሁኔታ የሕወሓት 27 የአገዛዝ ዓመታት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል ፡፡ የባከነው ሀሳብ ፤ የባከነው የሰው ሃብት የአንድ ትውልድ እድሜ ነው፡፡ ሀገር ተጎድታለች ፡፡ የሕወሓት አመራር ከዚህ ድርጅታዊ ባህሪው ሳይሻሻል ከአራት ኪሎ ሾልኮ ወጣ፡፡ ሾልከው የወጣው ለማፈግፈግ እንመቸው እንጂ ድርጅቱ ስለተለወጠ አልነበረም፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ሚድያ፣ ገንዘብ፣ መዋቅርና ወታደር ያለው ብቸኛ ተቃዋሚ ሆኖ ይገኝ ነበር፡፡

ከሀገር አንድነት ጋር የተላተመና ወዳጆቹ ሁሉ የካዱት ብቸኛ ሀይል በመሆኑ ብቸኝነት ተረጋግቶ እንዳያስብ ስላደረገው ብዙ የለመደ ትንሽ ያገኘ ድርጅት ሆኖ ስለቆየ አሁን ያለበት ደረጃ ደርሶ ይገኛል፡፡ አባላቱን መስማት ተስኖት የሽብር ተግባር ላይ ተዘፍቆ ይገኛል ፡፡ ከጀርባው ያዘላቸው ሀይሎች የሚጋልቡት ከፍተኛ አመራር እጅ በመሆኑ አባላቱ ሁሉ እየሸሹት፤ ስለ አወዳደቁም እየዶለቱበት ያለ ድርጅት ይመስላል፡፡ በሀገር ውስጥም ይሁን በመላ ዓለም የሚገኘው ደጋፊው እያፈገፈገ አብረው የበሉ አጃቢዎቹ የምንተ እፍረታቸውን እያጓሩ ያሉበትን ሁኔታ ኢትዮጵያውያን እየታዘብን እንገኛለን፡፡ ለውጡ እንዲመጣ እኔም አብሬ ወስኛለሁ የሚለው ድርጅት ትናንት መልምሎ ካሳደጋቸው ምልምሎቹ ጋር መስማማት አቅቶት በሽንፈት በሽታ እየተሰቃ ያለ መቀመቅ ውስጥ የገባ ድርጅት ሆኗል፡፡

በምስል ደረጃ የሃገራችንን ምስልንም ጭቃ ለመቀባት እየሞከረ ይገኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ ድርጅቱ ተቃዋሚ መሆን ሳይችል ቀርቷል፤ ሌሎችን ተቃዋሚዎችም ማስጠጋት አቅቶት፤ ትናንት በሰፈረው ቁና ለመሰፈር በራሱ ግዜ ከኢትዮጵያዊነት ቋጢኝ ጋር እየተላተመ ይገኛል፡፡ ይህን ሃብት እና እድል ይዞ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ትንሳኤ ለማምጣት ሊጠቀምበት ሲገባ ሀይሉን እያባከነ ብቻ ሳይሆን እውነተኛ ባህሪው ተገልጦ የሕዝብን ጠባቂ ሰራዊት የሚረሽን ሽብርተኛ ድርጅት ሆኖ ይገኛል ፡፡ ተፈጥሮውም ሆኖ ምርጫው ነውና ምንም ማድረግ አይቻልም፡፡

## ለምን እዚህ ደረሰ?

ኢትዮጵያ የትግራይን ሕዝብ ረስታ ቆይታለች፡፡ በትግራይ ብቸኛ አድራጊ ፈጣሪ ሕወሓት ብቻ ነበር፡፡ የትግራይን ሕዝብ በመረገጥ እና ከመሀል ሀገሩ ሕዝብ እንዲገለል በማድረግ በኩል ኢህአዴግ (የግንባሩ አባል ድርጅቶች) እና አጋሮች ከፍተኛ ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል፡፡ ‹‹እንወክለዋለን›› የሚሉትን ሕዝብ ከማስረገጥ እና ከማስበዝበዝ አልፈው በወዶገብነት ስለ ትግራይ ሕዝብ ጉዳይ ትንፍሽ ብለው እንደማያውቁ ድርጊታቸው ይናገራል ፡፡ ግማሽ ክፍለ ዘመን ለሚጠጋ ግዜ ትግራይን ተቆጣጥሮ የደለበ ገዥ መደብ ፈጥሯል፡፡ ቤተሰብ ድረስ የዘለቀ መዋቅር ዘርግቷል፡፡ እንደ ዘንዶ በትግራይ እና በትግራይ ሕዝብ ተጠምጥሞ በብቸኝነት ሲያሰቃየው ኑሯል፡፡ እናም ትግራይ በሌላው ኢትዮጵያዊ ወገን ተረስታ ቆይታለች፡፡ የመሃል ሀገሩ ፖለቲካ እና ፖለቲከኞች እንዲሁም የመንግሥት አካላት አግለውት ቆይተዋል፡፡ ለሕወሓት ግዞት ተትቶ ቆይቷል፡፡ ዛሬ ሁኔታዎች ተቀይረዋል፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያውያን አይኖች ትግራይ ላይ ማነጣጠር ጀምረዋል፡፡ ትግራይ ላይ ላለፉት 46 ዓመታት የደረሰው ቁስል ማመርቀዝ ጀምሯል፡፡ የትግራይ ልጆች በያሉበት ሲታገሉ ቆይተዋል፡፡ ቁስሉ ከሀብት ዘረፋ ጋር በመቆራኘቱ፤ ድርጅቱ ፀረ-ለውጥ እና ቆሞቀር በመሆኑ ለውጥ ፈላጊው የትግራይ ሕዝብ በሰፊው ለለውጥ እየተነሳ ይመስላል፡፡ የመሀል ሀገሩ የኢህአዴግ ሽክም ሲቀልለት እና ያለውን አንፃራዊ ነፃነት በመመልከት ራሱን ለትግል እያነሳሳ ይገኛል፡፡ ትግራይ ውስጥ የአፈና አይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ የትግሉ አይነትም መለያየቱ ግድ ነው፡፡ በዚህም ይመስላል ትግራይ ውስጥ እየተከሰቱ ያሉ ትግሎች የሚለያዩት፡፡ ‹‹ፈንቅል›› የተሰኘ በወጣቶች የተደራጀና በመደራጀት ላይ ያለ ሕዝባዊ የትግል ቡድንም ተከስቶ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት አዳዲስ ክሰተቶች መከሰታቸውም አይቀሬ ነው ፡፡

በኔ ሚዛን ካደረሰብን ጉዳት አኳያ ስመዝነው ሕወሓት/ኢህአዴግ መጥፋት/መፍረስ ያለበት ድርጅት ነው ብየ ካመንኩ ቆይቻለሁ፡፡ ኢህአዴግ ፈርሷል፡፡ ሕወሓት ብልፅግና ውስጥ ገብቶ አለመፍረሱ እሰየው ነው፡፡ የተሻለውን ባለመምረጡ የራሱ ጉዳይ ነው፡፡ ያ እድል አምልጦታል፡፡ አሁንም መፍረስ አለበት፡፡ ሆኖም ድርጅቱን በማፍረስ በኩል የቅድሚያ ሚናውን መወጣት ያለበት የትግራይ ወጣት የሚል እምነት ነበር፡፡ ሕወሓትን ማስወገድ የትግራይ ሕዝብ ጉዳይ ነው የሚል እምነት ነበር ፡፡ የትግራይ ወጣት ስል እነሱ የፈጠሩት አልቃሻ የትውልድ ክፍል ማለቴ አይደለም፡፡ እነሱ የፈጠሩት አልቃሻ ሚድያ ባለቤት፤ አልቃሻ አንቂ ነኝ ባዩን አይደለም፡፡ አልቃሻ ምሁርና አልቃሻው ነጋዴ አይደለም፡፡ ይህ በታሪክ ያለፉን ክስተቶች እያመነዠገ ሙሾ የሚያወርድ አልቃሻ፤ መጪውም የሚያስፈራው በርጋጊና ደንባራ ከሕወሓት ዙሪያ የተኮለኮለውን ትውልድ አይደለም፡፡ ይህ አብሮ መፍረስ ያለበት፤ በፍርስራሹ ላይ ታሪክ የሚሰራበት እና በስህተቱ ሲያፍር የሚኖር የትውልድ ክፍል ነው፡፡ ይህ የሕወሓትን አመራር መለወጥ የቤት ስራ ለትግራይ ሕዝብ መተዉ ተገቢ እምነት ነበር፡፡ ሕወሓት ግን ሀገርን የሚያፈርስ፤ አንድነትን የሚያናጉ በርካታ ጥፋቶችን መፈፀም የእለት ተእለት ተግባራቱ ሆኑ ፡፡

በዚህ ሂደት የቀድሞ የኢህአዴግ ግንባር አባላት እና አጋሮች የመሰረቱት ብልፅግና እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግሥት አካለት ሕወሓትን በማጀብ እንወክለዋለን ከሚሉት ሕዝብ በተጨማሪ የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት በብቸኝነት እንዲረገጥ ሊፈርዱበት አልተቻላቸውም፡፡ ትግራይም የኛ ነው ማለት ጀመሩ፡፡ ይከፋም ይልማ የትግራይ ሕዝብም ለውጥ ያስፈልገዋል በማለት በአደባባይም መስበክ ጀመሩ፡፡ ወጣቱም መብቶቼን የመጠየቅ ምልክቶችን አሳየ፡፡ እናም የመደራጀት መጥፎ አርአያ ሆኑበት፡፡ ወጣቱ ተደራጅቶ ከስልጣን ማማው እንደሚገፋው ሕወሓት ተረዳ ፡፡ በመሆኑም ፈሪው እና ጨካኙ ድርጅት ፍርሃቱ ጨመረ ፡፡ መደራጀት እና ፍትህ መጠየቅ ሕወሓት በበላይነት ባረቀቀው ሕገ-መንግሥት መብት ነው፡፡ ሆኖም በተከታታይ ራሱ ያጸደቀውን ሕገ-መንግስት መናድ ጀመረ፡፡ ይህም አልበቃውምና ፊቱን ከ20 ዓመታት በላይ የትግራይን ሕዝበ እና ሀገርን ሲጠብቅ ወደነበረው መከላከያ ኃይል ፊቱን አዞረ ፡፡ በውድቅት ሌሊት ጥቃት ሰንዝሮ ሠራዊቱ የታጠቀውን መሳሪ መዝረፍና ለልዩ ሃይሉ ማስታጠቁን በይፋ እየለፈፈ ይገኛል ፡፡ መከላከያው ራሱን መከላከል ሕጋዊ መብቱ ነውና ጥቃት በመሰንዘር ፤ የፌደራል መንግሥትም ሕዝቡን እና ሀገርን መከላከል ግዴታው ነውና ግጭቱ በሕወሓት ተጀምሮ እዚህ ደረጃ ደርሷል፡፡ ራስን መከላከል እንዲሁም ሃገርን የመጠበቅ ኃላፊነት በመከላከያ ትከሻ ላይ ወድቆ ይገኛል፡፡ ሀገሬን እወዳለሁ የሚል ዜጋ ሁሉ ይህን ፍትሀዊ የጥቃት ቅልበሳ ሊደገፍ የሚገባው ደረጃ ላይ አንገኛለን ፡፡

## ግጭቱ ምን ያስከትላል ?

ይህ እየተካሄደ ያለው ግጭት አንዳንዴ በወጣትነት እድሜ እንደሚከሰተው የሰፈር ልጆች የቡድን ግጭት አይደለም፡፡ የሰፈር ልጆች ግጭት ፈጥረው ድንጋይ ሲወራወሩ እንኳን መፈንከት ይኖራል፡፡ ከሚወራወሩት መሃል ብቻ ሳይሆን አልፎ የሚሄድ አልያም ገላጋይም ሊጎዳ ይችላል፡፡ ይህ ግጭት ራሱን ለበርካታ ዓመታት ሲያደራጅ በኖረ ቡድን እና በመከላከያ/በመንግሥት መካከል የሚደረግ እንደመሆኑ ተፅእኖዎች ይኖራሉ፡፡ በሀገርም በክልሉም የሚፈጥረው ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተፅእኖዎች ይጠበቃል፡፡

ኤፈርት ትልቁ የድርጅቱ (የሕወሓት) አንዱ የሃብት ምንጭ ነው፡፡ በርካታ ሰራተኞችን ከማስተዳደሩም በላይ ግዙፍ የባንክ እዳ የተሸከመ የሕዝብ ሳይሆን ሕወሓት የሚቆጣጠረው የንግድ ድርጅት ነው፡፡ ከሠራተኛውም ይሁን ከድርጅቱ የሚደርሰው ኪሳራ ቀውስ መፍጠሩ አይቀርም፡፡ በርካታ የክልሉ የመንግሥት እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም በችግሩ ምክንያት ሥራ የማይሰሩበት ሁኔታ ይከተላል፡፡ ሥራ ሲቆም ኢኮኖሚው ብቻ ሳይሆን ማኅበራዊ ቀውስም ይፈጠራል፡፡ በተጨማሪም በርካታ የክልሉ ነዋሪ ሕዝብ በምግብ ዋስትና ታቅፈው የሚኖሩበት የሀገራችን ክፍል መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ግጭት ሳቢያ የእለት ተእለት ስራዎች ስለሚቆሙ ወደ ተረጂነት የሚንሸራተቱ ወገኖች ይኖራሉ፡፡ የግል ባለሃብቱም ቢሆን በዚህ ግጭት ስር ሆኖ ማምረትም መገበያየተም አይቻለውም፡፡ ጉዞው የቁልቁለት ይሆንበታል፡፡ ገበሬውም ተጎጂው አካል ይሆናል፡፡ ትግራይ ካላት ሕዝብ ውስጥ በበርካታ ሺዎች የሚቆጠር የታጠቀ ልዩ ሃይል እና ሚሊሻ እንዳለ የሚያነሱ ወገኖች አሉ፡፡ ይህ ሀይል ከተሸነፈም በኋላ የኢኮኖሚው እና የማኅበራዊ ቀውሱ አካል እንደሚሆን ይታወቃል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ሸክሙ ይከብዳል ፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ይህን ሸክም የሚሸከመው ግጭቱን የለኮሰው ሕውሓት ሲሆን ቆይቶም ቢሆን ለሀገር የሚተርፍ እዳ እንደመሆኑ የመንግሥት ኃላፊነት ከፍ ይላል፡፡ ግጭቱ ጊዜ በወሰደ ቁጥር ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ቀውስ ስለሚጨምር የሚከተለውን ቀውስ ለመቀነስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድነት ቆሞ መከላከያንና መንግሥትን ሊደገፍ ይገባል፡፡ ይህ ሲሆን ነው የግጭቱ ግዜ ቀንሶ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሸክሙን ማቅለል የሚቻለው ፡፡

## ቀጣይ እርምጃዎች የሕወሓት መጨረሻ

ብልፅግና አዲስ ፓርቲ አይደለም ፡፡ ብልፅግና ውስጥ በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ (ዶ/ር) የሚመራ አዲስ አስተሳሰብ የሚያራመድ ቡድን እንዳለ ይታወቃል፡፡ ሆኖም አብዛኛው የብልፅግና አባል በቀድሞው ሕወሓት/ኢህአዴግ ባህል የተቀረፀ መሆኑ አይካድም፡፡ ዴሞክራሲን ለማዋለድ ሁለት እንቅፋቶች እያስተዋልን ነው፡፡ አንዱ እንደ ድርጅት ግጭት ውስጥ የገባው ከፍተኛው የሕወሓት አመራር ሲሆን ሁለተኛው ቀድሞ የተረጨው አስተሳሰብ ያልተላቀቀው የብልፅግና ካድሬ ይሆናል ፡፡ በሌላ አነጋገር አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ ብሔርተኝነት

ለአንድነታችን አደጋዎች ናቸው፡፡ ሕወሓት አሰላለፉ እንዲሁም ድርጅታዊ ባህሪውም ስለማይፈቅድለት ከአንድነት ሀይሎች ጋር ብቻ ሳይሆን ከቢጤዎቹም ጋር መላተሙ አልቀረም፡፡ በሂደት የሆነውም ይኸው ነው፡፡ ስለመገንጠል የሚዘምሩ ሀይሎችን ከጀርባው ተሸክሞ፤ የኢትዮጵያን አንድነት እየተፈታተነ የትግራይ ሕዝብ እንዲሁም መከላከያችን ሊሸከመው ስለማይችል የለየለት ትርምስ ውስጥ ገብቶ ይገኛል፡፡ የለኮሰው ግጭትም ፍትሀዊ ባለመሆኑ ሕዝባዊ መሰረት የለውም ፡፡ ስለዚህም ራሱን ከመብላት በዘለለ ትርፍ አይኖረውም ፡፡

ብልፅግና አብዮታዊ ዲሞክረሲን ነቅሎ በመጣሉ ለሀገራችን ባለውለታ ነው ፡፡ ያልተነቀለው በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ብሔርተኝነት ነው፡፡ ይህ መርዝ ብልፅግና ውስጥም ይንፀባረቃል ፡፡ ዛሬም ሕዝብን ማሰቃየት የሚችል ጉልበት አለው፡፡ ይህ የብሔርተኝነት መርዝ የሚነቀለው ከሕወሓት አመራር መነቀል ጋር ይሆናል የሚል እምነት የበርካታ ወገኖች እምነት ሆኖ ይገኛል ፡፡ የግጭቱ ዋንኛ ውጤትም ይህ መሆን ይገባዋል፡፡ መንግሥት ‹‹የሕግ ማስከበር እርምጃው አላማ ስግብግቡን የመቀሌ ጁንታ ለሕግ ተገዥ የማድረግ እና ሕገ-መንግሥታዊ ስርአትን ማስጠበቅ ነው፡፡ ይህ እርምጃ ከማንም በላይ ሰፊውን ትግራዋይ ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው›› የሚል አቋም አለው፡፡ ትግራዋይ ከማንም በላይ ተጠቃሚ የሚሆነው ግን በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ማንነትና አብዮታዊ ዴሞክራሲ በአንድ ላይ ከትግራይ ሲነቀሉ ነው፡፡ የነዚህ ችግሮች ምንጩ ደግሞ በዋነኝነት ሕገ-መንግሥቱ መሆኑ የብዙዎች እምነት ሆኖ ይገኛል፡፡ ከግጭቱ ማብቃት በኋላ እውነተኛ የሕዝብ ወኪሎች ተመርጠው አጠቃላይ ሕዝቡም ተወያይቶበት የሕገ-መንግሥት ማሻሻያ ተደርጎ ዜጎች የሀገራቸው ባለቤት ካልሆኑ አላማውን የሳተና የባከነ ግጭት ይሆናል፡፡ በዚህ ወሳኝ ወቅት ግን በብልፅግናም ይሁን በሌሎች ፓርቲዎች ውስጥ የሚንፀባረቀው በቋንቋ ላይ የተመሰረተው ማንነት ተነቅሎ ብዛህነቷን ያከበረች፣ የዜጎቿ የሆነች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ሁሉም ሀገር ወዳድ ከመከላከያና መንግሥት ጎን ሊቆም ይገባል! በግጭቱ ውጤት በቋንቋ ላይ ለተመሰረተው ማንነት እድሜ ቅጥያ እንዲኖረው ከተደረገ የመንግሥት ታሪካዊ ስህተትና ተጠያቂነት ሆኖ ያልፋል ፡፡ በትግራይ ሕዝብ ላይ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ተጭኖ ለኖረው ግፍ፤ ብቸኝነት እና ሰቆቃም ተጨማሪ ዓመታትን የመፍቀድ ጭካኔ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

# አብዛኞቹ የአሰሪዎች ኤጀንሲዎች በርካታ በሆኑ ሠራተኞች ላይ እያደረጉ ያሉት በደል እንዲቆም እንጠይቃለን !

ከኢዜማ የሙያ ማኅበራት ኮሚቴ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

ኢዜማ ለሠራተኞች መብት የቆመ መሆኑን ያረጋገጠው ካሉት ቋሚ ኮሚቴዎች አንዱን የሙያ ማኅበራት ዘርፍ ብሎ በመሰየሙ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የፓርቲ ፖለቲካ ታሪክ የሙያ ማኅበራት የሚል መዋቅር የነበረው ፓርቲ የለም፡፡ በአንዲት ሀገር የዴሞክራሲ ሥርዓት እውን መሆን የሠራተኛው ሚና ወደር የለሽ ነው፡፡ ሠራተኛው እንደተለመደው የመንግሥት የፖለቲካ ስርዓትን በካድሬነት አገልጋይ እንዲሆን ኢዜማ አይፈቅድም፡፡ የኢዜማ መርህ ሠራተኛው ለመብቱ የመቆም አቅጣጫ ያላቸውን ፓርቲዎች በመለየት ድጋፍ መስጠት እንዲችሉ ግፊት ማድረግ ነው፡፡ በአሰሪዎች ኤጀንሲዎች እየደረሰ ያለውን በደል ፓርቲያችን በሚገባ ተገንዝቧል፡፡

የአሰሪዎች ኤጀንሲ አሰራር በአገራችን መታየት ከጀመረ ዓመታት ተቆጥሯል ፡፡ በአውሮፓና ባደጉ ሀገራት ሠራተኛን ለሶስተኛ ወገን ቀጥሮ ማሰራት (Outsourcing) የኤጀንሲነት ሥራ የተቀላጠፈ አሰራርን የሚዘረጋ፣ የአሰሪዎችን የቢሮክራሲ ጭነት የሚቀንስ ብሎም ዘመናዊ አሰራር እንደሆነ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በአገራችን የሚገኙት አብዛኞቹ ኤጀንሲዎች በሕግ ፍቃድ የተሰጣቸው በሠራተኛው ላይ በደል እየፈፀሙ የሚገኙ ናቸው፡፡ ሠራተኛው ከአሰሪው ጋር ያለው ግንኙነት ሙሉ በሙሉ በኤጀንሲው ባለቤቶች እጅ የወደቀ ነው፡፡ ብዙዎቹ ሠራተኞች በማኅበር ያልተደራጁ በመሆናቸው ከአሰሪው ጋር የሚተዳደሩበት የሕብረት ስምምነት የላቸውም፡፡ በማኅበር የተደራጁ ጥቂት ሠራተኞች ቢኖሩም በአሰሪዎቹ የግፍ ቀንበር ሥር ተጠምደው የመከራ ገፈት እየቀመሱ ነው፡፡

አብዛኞቹ ኤጀንሲዎች ሠራተኛውን ወደ አሰሪው በመውሰድ ከአሰሪው የሚከፈለውን ደሞዝ አብዛኛውን ገንዘብ ለራሳቸው በመጠቀም፤ በዚህ የኑሮ ውድነቱ ጣሪያ በነካበት ዘመን የመከራ ኑሯቸውን እንዲገፉ ተፈርዶባቸው እየተሰቃዩ ይገኛሉ፡፡ በደሉ ጣሪያ እየነካ በመምጣቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሠራተኞች በብዙ ኤጀንሲዎች ላይ ተቃውሟቸውን በማሰማት ላይ ናቸው፡፡ ይህን ግፍ እየፈፀሙ ያሉት ጡረታ ከወጡ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የተውጣጡ ቤተሰቦች በሚመሩ የኤጀንሲ ባለቤቶች መሆኑን ሠራተኞች አበክረው ገልፀዋል፡፡ መብታቸውን ለማስከበር በቡድንም ሆነ በግል የተንቀሳቀሱ የኤጀንሲው ሠራተኞች ለጥቃት መጋለጣቸውን ለሕዝብ ይፋ አድርገዋል፡፡

ኢዜማ በአብዛኞቹ ኤጀንሲዎች በሠራተኛው ላይ ከፍተኛ በደል እያደረሱ መሆናቸውን ተገንዝቧል፡፡ ይህም ችግር እንዲፈታ መንግሥት ስህተት እየፈፀሙ ያሉ አብዛኛዎቹ ኤጀንሲዎች ላይ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የሠራተኛውን መብት እንዲያስከብር ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር ኮሚሽን (ኢሠማኮ) በአሰሪዎች ኤጀንሲ የሚደርሰውን በደል በተመለከተ በቂ መረጃ አለው የሚል እምነት አለን፡፡ መንግሥት የሰጠውን የ20/80 የደሞዝ አከፋፈል ባልተቀበሉት የሠራተኛ ኤጀንሲዎች ላይ መመሪያውን እንዲተገበሩ ግፊት ማድረግ አለበት ብለን እናምናለን፡፡





# የኢዜማ አባላት ለመከላከያ ሠራዊት አጋርነታቸውን እያሳዩ ይገኛሉ

ህዳር 2 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ምርጫ ወረዳዎች ለኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት አጋርነታቸውን እየገለፁ እንዳለ የምርጫ ወረዳዎቹ አስተባባሪ፣ ሊቀመንበርና ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ለዜጎች መድረክ አስታወቁ፡፡

የኢዜማ ወልዲያና ጉባላፍቶ ምርጫ ወረዳ አባላት ጥቅምት 28 ቀን 2013 ዓ.ም ራያ ግምባር ለሚገኘው የመከላከያ ሠራዊት 24 ደርዘን ውሃና በጎችን ይዘው በመቅረብ አጋርነት ማሳየታቸውን የሰሜን ወሎ የኢዜማ አስተባባሪ አማረ ስዩም ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡ አስተባባሪው ድጋፉን ማድረግ የፈለጉበትን ምክንያት ሲያስረዱም ሕግ ለማስከበር እየተደረገ ያለውን እርምጃ በመደገፍ ከመከላከያ ሠራዊት ጎን በመቆም አጋርነታችንን ለማሳየት ነው ብለዋል ፡፡ ድጋፉን ያደረጉት የኢዜማ ወልዲያና ጉባላፍቶ ምርጫ ወረዳ አባላት ከገንዘብ እስከ ሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ የዞኑ አስተዳደር ሎጂስትክ የሚያስተባብሩ ሰዎች ጠይቋቸው ሁለት ሰዎችን ከምርጫ ወረዳቸው ወክለው መላካቸውንም ጠቁመዋል፡፡ በተመሳሳይ ጥቅምት 28 ቀን 2013 ዓ.ም የኢዜማ ላይ አርማጮሆ ምርጫ ወረዳ አባላት ጠገዴ ወረዳ ላለው የመከላከያ ሠራዊት የአካባቢውን ማኅበረሰብ በማስተባበር ግምታቸው 50 ሺህ ብር የሆኑ 4 ሰንጋዎችን ማበርከት መቻላቸውን የላይ አርማጮህ ምርጫ ወረዳ ሊቀመንበር የሆኑት እያዩ ተኮላ ለዜጎች መድረክ ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል ‹‹ደማችን ለመከላከያ ሠራዊታችን›› በሚል መሪ ቃል የኢዜማ የባሕር ዳር ምርጫ ወረዳ አባላት ደም መለገሳቸውን የምርጫ ወረዳው ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መንግሥቱ አማረ ለዝግጅት ክፍላችን አስታውቀዋል፡፡ መንግሥት ሕግ ለማስከበር በሕወሓት ላይ እየወሰደ ባለው እርምጃ ላይ ኢዜማ ከጎኑ እንደሚቆም ማረጋገጡን ያስታወሱት ኃላፊው፣ ሠራዊቱ ሕግ በማስከበር እርምጃ ውስጥ ደሙን እያፈሰሰ ስለሚገኝ፣ በዚህ የተነሳም የደም እጥረት ሊከሰት ስለሚችል በሚል አባሎቻቸውንና ደጋፊዎቻቸውን በማስተባበር ከ250 በላይ ሰዎች ደም እንዲለግሱ ማድረግ መቻላቸውን አስረድተዋል፡፡ በቀጣይነትም ኮሚቴ አዋቅረው ሎጂስቲክ የማሰባሰብ ሥራ እንደሚሰሩ ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ጠቁመዋል፡፡ በተመሳሳይ በአዲስ አበበ ከተማ የሚገኘው የኢዜማ ምርጫ ወረዳ 17 አባላት ‹‹ደማችን ለመከላከያ ሠራዊታችን›› በሚል መሪ ቃል ጥቅምት 29 ቀን 2012 ዓ.ም በቀይ መስቀል ደም ባንክ በመገኘት ደም ለግሰዋል፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) ጥቅምት 26 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ የኢፌዴሪ መከላከያ ሠራዊት ለሚወስዳቸው እርምጃዎች የኢዜማ አባላት እና አመራር ሙሉ በሙሉ ከጎኑ እንደሚቆሙ ማስታወቁ አይዘነጋም፡፡

# < <የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያወጣውን መስፈርት ያሟሉና ያላሟሉ ፓርቲዎች በመለየት ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት> >

## ዋሲሁን ተስፋዬ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ



ህዳር 2 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ) የኢትዮጵያብሔራዊምርጫቦርድ መስፈርት ያላሟሉ ፓርቲዎች መሰረዝ እንዳለባቸውና ቦርዱ፣ ያወጣቸውን መስፈርቶች የሚያሟሉና የማያሟሉ ፓርቲዎችን ለይቶ ለሕዝብ ማሳወቅ እንዳለበት የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ ተናገሩ፡፡

«በአዲሱ የምርጫ ቦርድ አዋጅ የተጠቀሰውን መስፈርት ያላሟላ ፓርቲ የመለየትና ያላሟሉትን የመሰረዙ ስራ የምርጫ ቦርድ ነው» ያሉት ኃላፊው ቦርዱ ያሟሉትንና ያላሟሉትን ፓርቲዎች በመለየት ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት ብለዋል፡፡ ሂደቱ መዘግየቱን የጠቆሙት ዋሲሁን ተስፋዬ፣ በያዝነው ዓመት ምርጫ እንደመካሄዱ መጠን ቦርዱ የኮሮና ወረርሽኝ ከመግባቱ በፊት የጀመረውን ሥራውን እስካሁን አጠናቆ የትኞቹ ፓርቲዎች ናቸው ወደ ምርጫ የሚገቡት? የትኞቹስ ነው ቦርዱ ያወጣውን መስፈርት የሚያሟሉት? የሚለውን ምርጫ ቦርድ ከወዲሁ አጣርቶ በፍጥነት ለሕዝብ ማሳወቅ አለበት ብለዋል፡፡

በአዲሱ አዋጅ መሰረት የሀገር አቀፍ ፓርቲና የክልል ፓርቲነት መስፈርት የሚያሟሉ ፓርቲዎች ተለይተው መታወቅ አለበት ያሉት ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው፣ በቀድሞ አዋጅ የተመዘገቡ ከመቶ በላይ የሚሆኑ ፓርቲዎች ፓርቲ እየተባሉ መቀጠል የለባቸውም ብለዋል፡፡ »መስፈርቱን ያሟላው ካላሟለው መለየት መቻል አለበት፡፡ ቦርዱ ይህንን ኃላፊነቱን መወጣት ስላለበት ይህንኑ ኃላፊነቱን በፍጥነት ይወጣ» ሲሉ አሳስበዋል ፡፡

በአዲሱ የምርጫ ቦርድ አዋጅ መሰረት ሀገር አቀፍ ፓርቲ 10ሺህ ፊርማዎችን ማሰባሰብ ሲኖርበት የክልል ፓርቲ 4ሺህ ፊርማዎችን አሰባስቦ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡ ኢዜማ፣ ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ለቦርዱ ማቅረቡን ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ





# በወላይታ ዞን ሳይካሄድ የቀረው ስልጠና የፊታችን እሁድ ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል

ህዳር 2 ቀን 2013ዓ.ም (የዜጎች መድረክ)

ባሳላፍነው እሁድ ጥቅምት 29 ቀን 2013 ዓ.ም በወላይታ ዞን፣ ሶዶ ከተማ ሊሰጥ ታቅዶ ሳይሰጥ የቀረው ስልጠና የፊታችን እሁድ ሕዳር 06 ቀን 2013 ዓ.ም እንደሚካሄድ የኢዜማ ድርጅት ጉዳይ ኃላፊ ዋሲሁን ተስፋዬ ለዜጎች መድረክ አስታወቁ፡፡

ጥቅምት 29 ቀን 2013 ዓ.ም በወላይታ ዞን ሶዶ ከተማ ሊሰጥ የነበረውን ስልጠና የዞኑ አስተዳደር ባለመፍቀዱ የተነሳ ሳይካሄድ መቅረቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህንን ስልጠና የፊታችን እሁድ ሕዳር 06 ቀን 2013 ዓ.ም ለማካሄድ ለወላይታ ዞን አስተዳደርና ለሶዶ ከተማ አስተዳደር ስልጠናው እንደሚካሄድ የሚገልፅ ደብዳቤ እንዲገባ መደረጉን ድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡ «ሰላማዊ ሰልፍ እንጂ ስልጠናም ሆነ ስብሰባ ለማካሄድ ማሳወቅ የማይጠበቅ ስለሆነ ለዞኑ አስተዳደርም ሆነ ለከተማው አስተዳደር በደብዳቤ ማሳወቅ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድነው?» በሚል ከዜጎች መድረክ ለተነሳው ጥያቄ ኃላፊው በሰጡት ምላሽ ደብዳቤውን ማስገባት ያስፈለገው ዞኑ ላይ የነበረና የሚታወቅ የፀጥታ ችግር ስላለ የፀጥታ ችግር የሚከሰት ከሆነ እንዲያውቁት ለማድረግ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህ ዜና እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ለደብዳቤው ምላሽ ባያገኙም ስልጠናውን የፊታችን እሁድ እንደሚያካሄዱት አስታውቀዋል፡፡

ስልጠናው የሚሰጠው ከየወረዳው ለተውጣጡ ሊቀመናብርት፣ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣ የሕዝብ ግንኙነትና የፋይናንስ ኃላፊ አማካኝነት ነው፡፡ ስልጠናው አላማም ኢዜማ ሀገር አቀፉን ምርጫ እንዴት ያየዋል? ከምርጫ ዝግጅት አንፃር ምርጫ ወረዳዎች ማሟላት የሚገባቸው ነገሮች ምንድናቸው? ምንስ መስራት ይጠበቅባቸዋል? በሚለው ነጥብ ዙሪያ እንደሆነ ከድርጅት ጉዳይ ያገኘነው መረጃ ያስረዳል፡፡